


ዋለልኝ መኰንን

# <u>አሁንም ውድድሩን የዩኒቨርስቲ ተማሪ አሸነፈ</u>

**<የአዚናራ እስረኛ>** በሚል አርእስት ለተሰጠው የምርጥ ጽሑፍ ውድድር ለ፪ኛ ጊዜ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ወጣት አሸንፏል። በዚሁ ውድድር በዳኞች ነጥብ **<u>፩ኛነትን ያገኘው</u>** **<u>ዋለልኝ መኰንን፤</u>** በብሔራዊ አገልግሎት በጂማ ከተማ እንደሚገኝ በአድራሻው ለመረዳት ተችሏል። ዳኞቹ በሥነ ጽሑፍ ዝንባሌያቸው ከውጪ የተመረጡ ናቸው። ነጥብ ከመስጠታቸው በፊት የተወዳዳሪው ስም አይገለጥላቸውም። ሽልማት የሌለውን ነገር ግን የዛሬ ሳምንት የሚገለጠውን የ፪ኛነት ማዕረግ ያገኘው እንደዚሁ ተማሪ ጌታቸው በቀለ ነው።

**<u>ዋለልኝ መኰንን፤</u>** የመጽሐፉ ሽልማት፤ጅማ በሚገኘው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ጽሕፈት ቤት በኩል ሰሞኑን ይላክለታል። ፫ኛው ዙር ውድድር <የሲራራው ነጋዴ> በሚል አርእስት ነው። እንዳለፈው ጊዜ ሁሉ ልብ ወለድ ሆኖ ከ፩ሺህ ቃላት መብለጥ የለበትም።

የምርጥ ጽሑፍ ዝግጅት ፤

አዲስ ዘመን ጋዜጣ

ኅዳር ፲፰ ፲፱፻፷፩

# ምርጥ ጽሑፍ

# የአዚናራው እስረኛ

## ከዋለልኝ መኰንን፤ ብሔራዊ አገልግሎት

ጅማ

***ፈሪ ይኑር፤ ጐበዝ ይሙት ቢሻው***

***አተላ መሸከም ይወዳል ትከሻው***

ይኸን ፤ ተዝካር ሲቀር በየድግሱ ቡከኑም ፤ ጀግናውም፤ ወጣቱም ፤ ሽማግሌውም ፤ ጌሾ ራስ ሲመታ አባም ፤ ሴቷም ትለዋለች ። አዎ/ በሰላም ቀን ምንም ፤ ምንም ማለት አይቸግርም ። ችግሩ ፤ ቀኑ ሲጨልም ነው። ያኔ ብቻ ነው ዓለም በሁለት የምትከፈል ጀግናና ፈሪ። ያኔ ዖታ ፤ ሀብት ፤ ሥልጣን ፤ የመለያ ምልክትነታቸውን ያጣሉ።--------------------

እጁ እርፍ መጨበጥ ከጀመረ አንሥቶ በሽማግሌዎች<የልጅ አዋቂ> በወጣቶችና በኰረዶች <ላም> እየተባለ ይጠራ የነበረው ጢሰኛው አጐቴ በዚያ ፀሐይ በቀትር በጠፋችበት ጊዜ ነበር ኰርማነቱን ያስመሰከረ። የሰላሙን ጊዜማ እጁ ከእርፍ ሳይላቀቅ ፤ ቀንጆ ሳይጨብጥ እንደ ሰው ሳይፎክር አረንዛ ሲፈነቅል ነው ያሳለፈ። <ላም> ሆኖ ሐያ ሦስት ዓመታት ኖረ ማለት ነው።

<ምታ ነጋሪት ከተት..........> ሲባል ከዚያች ከሰላም ቀን ጀግና መንደር አንድም ሰው እግሩን ሳያነሳ ቀረ። ከባላባት እስከ ጫቃ ሹም <ለመጣው ማደር ነው> እያለ ከብርጭቆው ጋር ጨዋታውን ቀጠለ። አጐቴ ብቻ በብሔራዊና በግላዊ ሐላፊነት መካከል ተወጥሮ ጤና አጣ። በአንድ በኩል ሰባ ዓመት የተሻገረ አባቱን ሲሶ አርሶ የመጦር አላፊነት ሲኖርበት በሌላ በኩል ደግሞ አገሩን ከውጭ ጠላት ፤ ሃይማኖቱን ከባዕድ አምልኮ ፤ ሚስቱን ከሰላቶ እንዲከላከል ቁሱ ተዝካር ላይ አውጀዋል።

ቤተክርስቲያን ሔዶ ባያውቅም ፤ ጊዜ አልነበረውም ። ሃይማኖተኛ ነው። የቤተክርስቲያን ሰዎች የሚሉትንም ይሰማል ይኸ ብቻ አይደለም ። ሠርግ ላይ በፉከራ፤ ከመጠጥ በኋላ በሽንት

ሳይተነፍስ ሳይቀዘቅዝ ታፍኖ የቆየው ወኔው ገነፈል። በጐራዳ ሚስቱ ጸንቶ በመኖሩ ያን ሽንጥ ለማቀፍ ዕድል በማጣታቸው የተበሳጩ ሴቶች <ነይ ውሃ እንቅዳ> ያሉት ትዝ አለው። ወንድነቱን ተጠራጠረው <አንቺ ባልሽ ከተጋደመ ይነቃል?> አሉኝ እነከበደ ብላ ተኝተው ሳለ ሚስቱ ስትነግረው ነገሩን ለማቃለል ሲል <ሴት መጥተህ አታዳምጥም በይው> ያለው ትዝ ሲለው አተኰሰው። አፋፍ ላይ ቆመው ሁሉንም አውጥቶ አውርዶ ሲጨርስ < ሚዛኑ አደላብህ አብዬ> ብሎ ከንፈሩን ነከሰ። መውጫና መውረጃውንም አሰበ። <የመሳሪያ ችግር የለም > <አለ ለራሱ። <የቀኛማችም አለ ። የከበደ ይሻል ይሆን? የለም አሰፋ እኮ የለም። ሚስቱ ወጣ ስትል የእሱን ልሰረቅ። ኩነኔ ይሆን? ይሁና! በእርፍ ከሚያስቀረኝ ለእኔስ አይሰጠኝም ኖሯል?> ብሎ ፊቱን ወደ መንደሩ መለሰ።

አጐቴ የባለርስቱን ልጅ የአስፋን ወጨፎ ሰርቆ ዓባይን ተሻግሮ ከራስ እምሩ / ዛሬ ልዑል ራስ / ጦር ጋር ተቀላቀለ።

ለአጭር ጊዜ የተሰጠውን የጦር ስልት ጥናት በሚገባ አጠናቅቆ ጥሩ ውጤት ስለአሳዬ ከወጨፎው ተለያየ። < ምን የመሰለች ቢውጧት እንኳን የማትጐረብጥ > እያለ ዛሬ ድረስ የሚያቀማጥላትን መካከለኛ ቤልጅግ ተቀበለ። ለመጀመሪያ ጊዜም የጥርሱ ፍንጭት ታየ። ከአንገቱም ቀና አለ።ዛሬ ጨዋታ ሲነሣ <ነብሱን ይማርና በቀልዬ--- ይል ነበር> ብሎ የሚተከዝለትን ጓደኛም አበጀ።

ዝግጅቱ ተጠናቅቆ ወደ ጦር ግንባር ጉዞ ተጀመረ። አጐቴ ከቀዳሚ ጦር መሃል ነበር። ወደ ጐጃም ሲሔድ ደፍርሶ ይፎክር የነበረውን ሲመለስ እንባ የደረቀበት አልቃሽ የመሰለውን ዓባይ አይዞህ ብሎት ተሻገረ ። በጠርዙ ላይ እንባ ያዘለው ጨፌ ሆዱን ቢያባባው ረመረመው። አዘን የተጐናጸፈ የሚመስለውን ተራራ ገላምጦ አለፈው። ለመድረስ እንደጓጓ፤ መድረስ አይቀርም ማይጨው ደረስ።

ጦሩ በአዛዥ በአዛዡ ከተከፈለ በኋላ ማጥቃቱ እንዲጀምር ታዘዘ። ከበቀለ ጋር ትከሻ ገጥመው ወደፊት ገሰገሱ ። ቦታ ይዘውም ማጥቃት ጀመሩ። ጦርነቱ ተፋፋመ። <የጠላት ጥይት እንደማሽላ ተንጣጣች። ቦምብ ከሰማይ ዘነበ። የተሰማ ልጅ ወይ ፍንከች > ይላል አጐቴ ዛሬ ሁኔታውን ሲያስታውስ። የጠላት ጦር አይሎ ወደ ፊት ገፋ ። በአጐቴ አባባል <የመጀመሪያውና የመጨረሻው አሳዛኝ ድርጊት ተፈጸመ። የመጀመሪያውና የመጨረሻው ጓደኛዬ ተመታ ። የምወዳትንና የምሳሳላትን ቤልጅጌን ወርውሬ የማፈቅረውን ፤ እንደ ዓይኔ ብሌን የምጠብቀውን ጓዴን ላነሣ ሮጥኩ ። ቀና አድርጌ ልቡን ባዳምጠው አይመታም ሞቷል። ለመበቀል ወደ ቤልጅጌ ዞር ብል የለም። ቀና ብል ባንዳ በደንደሴ አቅጣጫ የጠብመንጃውን አፈሙዝ አስተካክሎ ቆሟል ። <እጅ ወደ ላይ > ብሎ ሳይጨርስ የመርዶፋ ኪሴን ብርብራ

ያዘው። ጨርሶ <ሒድ! ሲለኝ ! ዛሬ ገና የተሰማ ልጅ ላም ሆነች> አልኩት ለራሴ። ስሔድና ስኖር ሳላውቀው ስመለስ ብቻ ወደ አወቅሁት ቦታ ተጓዝኩ። <አዚናራ>

ከዚያስ በኋላ ምን ሆነ አጐቴ? ስለው ወሬ ሲበቃው <የተሰማ ልጅ ላም ሆነ> ይልና ዝም ይላል። አዚናራ የሆነውን ይችን ጽሑፍ ሳዘጋጅ ብቻ በብዙ ልመና <አጐትዬ፤ የእኔ ጌታ፤ የተሰምዬ ልጅ(ሲሉት ይወዳል) አፈር ስሆን> ብዬ ለምኜ እንዲህ ሲል ተረከልኝ።

<አዚናራ ዙሪያዋን በውሃ የተከበበች ደሴት ናት። መሬቷ ገሐና ገጣጣ ሆኖ የንፉግ እንጀራ እናት ፊት ይመስላል። ያቺ የድሮ መጣፍህ እንዳለችው <ቀና ቢሉ ሰማይ፡ ጐንበስ ቢሉ ምድር------ ነው። ያውም የሚታየው በ፫ ቀን ፩ ቀን ለቁፋሮ ስንወጣ ነው። ያለዚያማ አንቀጥ፤ ጨለማ ፤ ሲኦል ውስጥ መታፈግ ነው። አየር የሚገኘው ሰው ሲሞት ብቻ ነው። ያውም በስንት ጩኸት። የሞተውን ለማስወጣት ፤ <ደግነቱ> ቶሎ ቶሎ ይሞታል። በሩ ሲከፈት ትንሽ ነፋስ ይገኛል። ያለዚያማ አሰልች ተራ መጠበቅ ነው። ----ሞቶ ለማስቆፈር ወይም የሞተውን ቆፍሮ ለመቅበር፤

<ምግብ ፤ ምግብ? አዎ ምግብ በቀን ፩ ጊዜ ነው። ደረቅ የማሽላ ቂጣ ከግማሽ ቆርቆሮ የጨው ውሃ ጋር የቡና ቁርስ ፤ ምሳና ራታችን ነው። <ከ ፳፬ ሰዓት ፲፰ቱን በሚያንገሸገሽ፤ በሚያሰለች፤ በማያልቅ ቁጭታ ያልቃል። አዚናራ ፤ ዓይነተኛ የእስረኛ ደመኛ ጊዜ ነው። ቢገፉት አይገፋ፤ በተረት ፤ በጨዋታ ቢያታልሉት አይታለል የማይነቃነቅ ውዝፍ ነገር ነው። እንደ እኔ መቀመጫው ሳይነካ ፤ <ና ውጣ ና ው -- ውረድ> ሲል ዕድሜውን ለጨረሰ ታታሪ ከመቀመጥ የበለጠ መቀጫ የለም። ቁንጫው ፤ ትኋኑ ፤ ርግጫው ፤ ጥፊው ፤ ጡጫው ፤ ፈለጣው፤ ቁፋሮው ተደምሮ በራሱ ቢበዛ እንደመቀመጥ አያመኝም ። አያስመርረኝም ። እንዲህ አንገሽግሾን ቁጭታው ሲያልቅ መቀመጫ ቦታውን ለጐን ይለቃል። እንዳይተኛ የለም። ደንጋይ አጥንትን ፤ አጥንት ድንጋይን እየቆረቆረው በመኻከል ነፍስ እየተሰቃየች ይነጋል። ቁንጫ ፤ ቅማልና ትኋን ይዘምታሉ--- ነግቶ እንደ ጣልያን ድል እስኪመቱ ድረስ <የሦስቱ የጨለማ ቀኖች እንዲህ አልፈው አራተኛው የብርሃን ቀን ሲመጣ ከሲኦል ምሕረት ተደርጎላት ገነት እንደገባች ነፍስ ወጪዎችን የደስታ ማዕበል ይውጠናል። ቀሪዎች በተራቸው ያዝናሉ። እንዲህም ስልህ ውጪው የሚያስደስት አይምሰልህ። በዚያ በቃጠሎ (ፀሐይም አዚናራ ስትደርስ ትቆጣለች መሰል ደሟ ይፈላል) ቋጥኝ አለት፤ ጥቁር ድንጋይ! ፍለጥ ይልሃል።፫ ሜትር ጉድጓድ ለራስህ መቀበሪያ ያስቆፍረሃል። ደከመኝ ቆረጠኝ ማለት የለም። <ደከመኝ> ማለት በጣሊያን <በለኝ> ማለት ነው መሰል ፤ ተናግረህ ሳትጨርስው ነው ያ ሰላቶ ባልተወለደ አንጀቱ የዱላ መዓት የሚያወርድብህ። ይህ ሁሉ ሆኖ ተራራውን ፤ ሜዳውን ፤ ቁልቁለቱን ፤ አቀበቱን ማየቱ ሲኦል አለመሆናችንንና እስር ቤት መሆናችንን ስለሚያረጋግጥልን

ነው መሰል ጨለማ ውስጥ ከመቀመጥ ሁላችንም ውጪ መውጣቱን እንመርጣለን። ውስጥ ስንሆን ሌላው ቀርቶ ርግጫው ይናፍቀን ነበር።

< አዚናራ በነበርነው እስረኞች መካከል መቀራረብም መራራቅም ነበር። ሁላችንም ለነፃነት ታጋዮች ነበርን። ይህ አንድ መመሳሰል ነው። ሁላችንም የጣልያን እስረኞች ነን። ሌላ የሚያስተሳስብ ነገር ፤ ዘራችን ከአበሻ ምድር ከየጐሳው ፤ ሌሎችም ዓረቦችና እንግሊዞች ነበሩ። የዘር ብቻ ሳይሆን የሃይማኖትም ልዩነት ነበር። ሆኖም የጋራ ዓላማና ጠላት ስለነበረን እንስማማ ነበር። ይኸው ስምምነታችን ነው ያችን የማትገበር የተፈጥሮ እስር ቤት የሆነች፤ አይጸዳሽ ፤ ማስከፊያ ደሴት ለቅቀን እንድንወጣ ያሳሰበን፤ በኋላም አሳባችንን ያስፈጸመልን።>

< አዚናራ ሁለት ዓመታት ያህል በደቂቀ ቹቹሊ ከአሰቃየችን በኋላ ሐያ ያህል የምንሆን ከሞት የተረፍንና ሞትን ቁጭ ብሎ መጠበቅ የሰለቸን እሥረኞች ተማክረን ሌሊት ሰብረን ወጣን። አራቱን የጠላት ጥይት ሲያስቀራቸው ሌሎቻችን አመለጥን። አዚናራም ከርሷ የማይጠበቅ ውለታ ዋለችልን። ጀልባ እስክናገኝ ድረስ ለሦስት ቀኖች ያህል ተራራ ሥር ካለው ጉያዋ አስቀምጣ ከተኲላ አዳነችን ። > በአሳብ ተውጬ አዚናራን ስቃኝ < አሁን ለምን አስታወስከኝ> ብሎ በብዙ ከተነፈስ በኋላ ዓይኖቹን በግራ እጁ እየጠረገ ቀኝ እጁን ጠላ ወደያዘችው ብርጭቆ ሲልክ ሰላቶ አንገቴን ሊይዝ እጁን የዘረጋ መስሎኝ ብንን አልኩ። የምለው ባጣ በል እንጂ አጐቴ ይህን ሁሉ ውለታ ለአገርህ ውለህ ለምን ማደርያ አልጠየክም ? አልኩት ።**<ውለታ?>** አለ ። <ለማን ነው የዋልኩት? የዋልኩለት ሰው ቢኖር እኔ ነኝ። ነፃነትን ባጣ ለነፃነቴ ተዋጋሁ። ነፃነቴ አገኘሁ ። ለነፃነት ለተዋጋ ሰው ከነፃነት የበለጠ ምን ዓይነት ሽልማትና ማደሪያ ያስፈገዋል? > አለኝ ። ከሲሶ እርሻ ብትወጣ ይሻልሃል ብዬ ነው እንጂ አልኩት እየፈራሁ> እኔ ለነፃነቴ ፤ ለቆዳዬ ነፃነት ተዋግቻለሁ ። ለመኖር ነፃነት ተጋድያለሁ፤ አረጀሁ ! ያፈሩን ትግል ለእናንተ ትቻለሁ። ከሲሶ እርሻ ብትወጣ ይሻልሃል ብዬ ነው አልከኝ? እውነትክን እኮ ነው (በማፌዝ)። እንደ አንተ አባት ለሰላቶ ዕንቁላል ባመላልስ እኮ እርግጥ አወ። ------ ነበር። እ---------እ! >